የበግዳዱ አበባ

አቡ ሙሐመድ ሙሕዪዲን በሁለቱም ወላጆቻቸው በኩል አህለል በይት (የነብዩ ሙሐመድ ሰለላሁ ዓለይሂ ወኣሊሂ ወሰለም ዘር) ናቸው። ከብዙ የማእረግ ስሞቻቸው መካከል 'አልሐሰኒ ወልሑሰይኒ' ይገኝበታል። በአባታቸው በኩል ከሐሰን ኢብን ዓሊ በእናታቸው ደግሞ ከሑሰይን ኢብን ዐሊ ረ.ዐ የዘር ግንድ ይመዘዛሉ። ሸይኹል መሻኢኽ ሰዪዱና ጁነይድ አልበግዳዲ ከሁለት መቶ አመታት በፊት ውልደታቸውን አበስረዋል። አንድ ቀን የበግዳዱ ጁነይድ ሩሓቸው መጥቃ (ፈናእ ውስጥ ገብተው በነበረበት) ጊዜ "እግሩ ከትከሻዬ በላይ ነው፡ እግሩ ከትከሻዬ በላይ ነው" አሉ። ዚክራቸውን እንዳጠናቀቁና ከዚህ ስሜት ቀዝቀዝ ብለው በረጉበት ሰአት ተማሪያቸው ምን እያሉ እንደነበር ጠየቃቸው። "በ5ኛው ክፍለዘመን ማብቂያ ላይ ትልቅ ወልይ ይወለዳል" ብለው አበሰሩ፡ "ስሙ አብዱልቃዲር ሲሆን መጠሪያው ሙሕዪዲን ይባላል። ጂላን ከተማ ተወልዶ በግዳድ መጥቶ ያብባል። በአላህ ትእዛዝ አንድ ቀን እንዲህ ሲል ይናገራል "እግሬ ከአላህ ወዳጆች ትከሻ በላይ ነው" ይላል። ይህን ክስተት አይቼ ነው ቅድም ቃላቶቹ ከቁጥጥሬ ውጭ ሆነው ከአፌ ያመለጡኝ" አሉ።

Edit with WPS Office

ረመዳን 470 ዓ.ሂ ኢራን ውስጥ ጂላን በምትባል ከተማ ከአባታቸው አቡ ሷሊህ ሙሳ እና ከእናታቸው ሰዬዳ ኡሙልኸይር ፋጢማ ተወለዱ። አባታቸው ገና በልጅነታቸው በማለፉ አያታቸው አብደላህ ሱማዒ ሊያሳድጓቸው ሆነ፤ ነገር ግን እርሳቸውም ብዙ ሳይቆዩ ወደ አኺራ ተሻገሩ። ሱልጧኑል አውሊያእን የማሳደግ ሀላፊነት እናታቸው ኡሙልኸይር ላይ ወደቀ። እናታቸው ሰዬዳ ፋጢማ እጅግ አላህን ፈሪ ነበሩ፡ ልጃቸውን በእውቀትና በመልካም ስብእና ኮትኩተው ገና በለጋነታቸው እንዲያብቡ አድርገዋል። ሸኽ አብዱልቃድር ጂላን ከልጅነታቸው ጀምሮ ጨዋታና ቀልድ አይስባቸውም ነበር። ከህፃንነታቸው ጀምረው አላህን እየዘከሩ በተመስጦ እያሰላሰሉ በተፈኩር ያሳልፋሉ።

ራሳቸው ስለ ልጅነት ጊዜያቸው ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ

‹‹ህፃን ልጅ ሳለሁ፡ አንድ መልከ መልካም ወጣት ይከታተለኝ ነበር። ሁልጊዜ ከአቅራቢያዬ አይጠፋም። ከቤቴ ወጥቼ ትምህርት ቤት ድረስ ስጓዝ አብሮኝ ይሄዳል፤ ከገባሁ በኋላም ከመጀመርያ ረድፍ ላይ ቦታ እንዲሰጡኝ ሸሪካዎቼን ያዛቸዋል። ሌሎች ተማሪዎች በአንድ ሳምንት የሚቀሩትን እኔ በአንድ ቀን አጠናቅቅ ነበር። ቀኑን ሙሉ አብሮኝ ይቆይና ምሽት ላይ ወደቤት ስመለስ ይሸኘኛል፤ ይህ ወጣት ማን እንደሆነ አላውቅም። አንድ ቀን ግን ማንነቱን ጠየቅኩት፡ ‹‹እኔ

Edit with WPS Office

ከአላህ መላእክቶች አንዱ ነኝ፤ ወዳንተ የላከኝ እሱ ነው፤ ትምህርት እስከምትጨርስ ድረስ አብሬህ እንድሆን ታዝዤ ነው›› አለኝ።

በልጅነቴ ልጆች ሲጫወቱ አብሬ ለመጫወት ሳስብ እንግዳ ድምፅ ይሰማኛል፤ ልክ ለጨዋታ ልወጣ ስል "ና ወደኔ" ይለኛል ‹‹እሱን ተወውና ወደ እኔ ና! አንተ የተባረክ ልጅ ና፡ ወደኔ›› የሚል ድምፅ ሲያስተጋባ እሰማለሁ። እንደዚህ በሚሆንበት ቀን ከእናቴ ጉያ መሸሸግ እመርጣለሁ።

"እዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊነት ደረጃ ለመድረስ ያበቃዎ ሚስጥር ምን ይሆን?" ተብለው በተጠየቁ ጊዜ ‹‹ለእናቴ የገባሁላት የእውነተኝነት ቃል ነው›› ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። በራሳቸው አንደበት ሲተርኩት እንደሚከተለው ሰፍሯል

‹‹በዒደል አድሃ ዋዜማ ነበር፤ መሬቱን ለማረስ ወደ እርሻ ቦታ ሄጃለሁ፤ በሬውን አጥምጄ ስራዬን እየሰራሁ ባለሁበት፡ በሬው ቆም አለና ዘወር ብሎ እየተመለከተኝ ‹አንተ ለዚህ አይደለም የተፈጠርከው› አለኝ። ተርበተበትኩ፤ ፍርሃት እያንቀጠቀጠኝ እየሮጥኩ ወደቤት ገባሁኝና ምንጣፍ ላይ ጥቅልል ብዬ ተኛሁ፤ ከዚያ ያለ አባት ወዳሳደገችኝ እናቴ ተሸሸግኩ።

‹‹እናቴ ወደ እውነት ምድር ላኪኝ፤ በግዳድ ሄጄ እውቀት

Edit with WPS Office

እንድቀስም ፍቀጂልኝ፡ ከጥበበኞች እና ለአላህ ቅርብ ከሆኑት ሰዎች ጋር እንድሆን ወደዛ ስደጂኝ›› አልኳት። እናቴ ደነገጠች፡ ‹‹ይህ ድንገተኛ ጥያቄ ምንድን ነው? ከየት የመጣ ሃሳብ ነው?›› አለችኝ። የሆነውን ሁሉ አጫወትኳት። እያለቀሰች ስታዳምጠኝ ቆይታ ጊዜው መድረሱን እሷም አወቀች። ቀጥላም አባቴ ሲሞት የተወልንን ሰማንያ የወርቅ ሳንቲሞችን ይዛ መጣችና ግማሹን ለወንድሜ አካፍላ አስቀረችው። የተቀረውን አርባ ዲናር ደግሞ ከልብሴ ጉያ ስር ሰፋችልኝ። ወደ በግዳድ እንድሄድ ፍቃዷን መርቃ ሰጠችኝ። ነገር ግን ጉዞ ከመውጣቴ በፊት አንድ ነገር ቃል እንድገባላት አደረገች፤ እሱም የተፈጠረ ነገር ቢፈጠር ከእውነት ውጪ ምንም ቃል እንዳልናገር ነበር። እዚህ ላይ ቃሌን ሰጥቻት ተለያየን። ‹‹የአላህ ጥበቃ እና ቅናቻ አይለይህ የኔ ልጅ! እኔ ዘንድ እጅግ ውድ የሆነውን (ልጄን) ለአላህ ስል አሳልፌ ሰጥቻለሁ። የመጨረሻው የፍርዱ ቀን እስከሚያገናኘን ድረስ እንደማላይህም አውቃለሁ›› ብላ ተሰናበተችኝ።

ወደ በግዳድ የሚሄድ አነስተኛ ቅፍለት ተጋርቼ መጓዝ ጀመርን፤ ሀመዳን ከተማን አልፈን እንደወጣን በድንገት ጠንካራ ፈረሰኛ ሽፍቶች ወረሩን። እያንዳንዱን ሰው እየፈተሹ ያለውን ንብረት በሙሉ ጠራርገው ይዘርፉ ጀመር። አንድኛቸው ወደኔ ቀረበና ‹‹አንተ ወጣት ምን ይዘሃል?›› አለኝ፤ አርባ የወርቅ ሳንቲሞች እንዳሉኝ ነገርኩት። የታሉ

Edit with WPS Office

ሲለኝ፡ ከልብሴ ጉያ ስር አሉ ብዬ ተናገርኩ። ከት ብሎ ሳቀና ትቶኝ አለፈ። ሌላኛወም መጣና ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቀኝ፡ እኔም እንደመጀመርያው ተመሳሳይ ምላሽ ሰጠሁ። እውነቱን ነው የተናገርኩት፡ ግን እሱም ጥሎኝ ሄደ። ከኔ ጋር የተፈጠረውን ለመሪያቸው ነገሩት መሰል አለቃቸው ያገኙትን ንብረት የሚከፋፈሉበት ቦታ ድረስ አስጠራኝ። የያዝኩት ነገር አለ እንደሆነ እሱም ጠየቀኝ፤ ከለበስኩት መጎናፀፍያ ስር አርባ የወርቅ ሳንቲሞች ተሰፍተው አሉ ብዬ ነገርኩት። ልብሴን አስወልቆ ሲፈትሽ ወርቆቹን በሙሉ አገኛቸው። እጅግ በጣም ተደነቀ፤ ‹‹ገንዘብህ አስተማማኝ ቦታ ተቀምጦ ሳለ፡ ለምን ለኛ መናገር፡ ቦታውን ማሳወቅ አስፈለገ?›› ሲል በአድናቆት ተገርሞ ጠየቀኝ

‹‹በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብሆን ከእውነት ውጪ አልናገርም፤ ለእናቴ ቃል ገብቼላታለሁ›› አልኩት። የሽፍቶቹ መሪ በመለስኩለት መልስ ልቡ ተነካ፤ ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር። ‹‹እኔ ለፈጠረኝ ጌታ የገባሁትን ቃል መጠበቅ አልቻልኩም፤ እየዘረፍኩ፣ እየገደልኩ ነው የኖርኩት። ወደፊት ምን ይገጥመኝ ይሆን?›› እያለ በፀፀት አነባ፤ ወደ አላህም ተመለሰ። በስሩ የነበሩ ሰዎች ‹‹እነዚህን ሁሉ አመታት በሰራነው ወንጀል መሪያችን ነበርክ፤ አሁን ደግሞ ወደ አላህ በመመለስ መሪያችን እንድትሆን እንፈልጋለን›› አሉ። ስልሳዎቹም ሰዎች እጄን ይዘው ተውበት ማድረጋቸውንና

Edit with WPS Office

የህይወት መስመር መቀየራቸውን ተናዘዙ። በኔ ምክንያት ለመጀመርያ ጊዜ ወደ አላህ የተመለሱ ሰዎች እነዚህ ናቸው፤ ለትልቅ ደረጃ የበቃሁትም እናቴን በመታዘዜ ምክንያት ነው››

በግዳድ

ከፖለቲካዊ ድባቡ ለመነሳት የሰልጁቅ፣ የቱርክማኖች፣ የመምሉኮች እና ሌሎች የአውራጃ ሙስሊም አማፂያን እያቆጠቆጡ ነው። የመራሄ መንግስቱ ወራሾች እርስበርስ መሻኮት ጀምረዋል። በቤተ-መንግስት የነበረው ነብያዊ ባህል ጠውልጓል። ኸሊፋዎች ከፍተኛ ቁሳዊ ጥም ውስጥ ተዘፍቀዋል። ቆነጃጅትን መርጦ ማግባት፣ በስልጣን ላይ ያላቸውን ቆይታ ለማራዘም ሲባል ሀጢአቶችን መፈፀም፣ ቃዲዎችን መጨቆን፣ የዲን ምሁራንን አለማክበር ወዘተ በስፋት ይታዩበት የነበረ ጊዜ ነበር።

ሱልጣኑል አውሊያእ አብዱልቃድር ጂላን 488 ዓ.ሂ በግዳድ ደረሱ፡ ኒዛሚያ መድረሳ ውስጥ የሚሰጡ ዒልሞችን ተፍሲር (የቁርአን ትርጉም)፣ ሀዲስ እና ሱና (የነብያችን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የህይወት መንገድ)፣ ፊቅህ (ኢስላማዊ ህግጋት) እና አረብኛ ተማሩ። ነገሮች አልጋ በአልጋ ሆነው አያውቁም፡ እሳቸውም በነዚህ ሂደቶች ውስጥ ብዙ ችግሮችን አሳልፈዋል። ወቅቱ የዐባሲያ ንግስና ዘመን እያበቃ

Edit with WPS Office

የነበረበት ጊዜ በመሆኑ መንግስት ለሀይማኖት ይሰጠው የነበረው ቦታ ደካማ፣ ሰዎችም ከእምነቱ ጋር ባላቸው ግንኙነት ከፍተኛ መራራቅ ተፈጥሮ ነበር። "በግዳድ ውስጥ እየተማርኩ በነበርኩበት ጊዜ ያጋጠሙኝ ችግሮችና መከራዎች ተራራ ላይ ቢጣሉ ኖሮ፡ ተራራው ለሁለት ይሰነጠቅ ነበር" ብለዋል። ይህን ያክል አሳር ቢያዩም የጀመሩትን መንገድ ግን ለመተው አስበው አያውቁም ነበር። "መከራው ብሶ የከበደኝ ጊዜ ወደ በግዳድ ሜዳዎች እሄድና በጀርባዬ ተንጋልዬ" ከችግርም ጋር ምቾት አልለ። ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አልለ" የሚለውን የአላህ ንግግር ደጋግሜ እቀራዋለሁ። ያን ጊዜ ቀለል ይለኝና እደሰታለሁ" ይላሉ ያሳለፉትን ህይወት ሲተርኩ።

አንድ ጊዜ ተማሪ እያሉ በግዳድ ውስጥ ከፍተኛ ድርቅ ተከሰተ። ሰዎች አንዲት ፍሬ የስንዴ ዘር ማግኘት ተቸገሩ። እህል ሲጠፋ ቅጠላ ቅጠል እና እፅዋቶችን መመገብ ተያያዙት። ገውሰል አዕዘም በዚህን ጊዜ እንደሰዎች ምግብ ፍለጋ ከከተማ ይወጣሉ፡ ነገር ግን የህዝቡን ምግብ ፍለጋ መንከራተት ሲመለከቱ እነሱ ከኔ በላይ ተቸግረዋል እያሉ ይመለሳሉ። በዚህ ሁኔታ እህል ሳይቀምሱ በርካታ ቀናት አለፉ። አንድ ቀን 'ሱቁር ረይሃነይን' ከተባለ ገበያ ስፍራ ምግብ ለመፈለግ ወጡ፡ ድካማቸው በርትቷል፣ መቆም እስኪያቅታቸው ድረስ ብዙ ቦታዎችን ዞሩ፡ ነገር ግን

Edit with WPS Office

የሚቀመስ ማግኘት አልቻሉም። በአቅራቢያቸው መስጂድ አገኙና ገብተው ከአንድ ጥግ አረፍ እንዳሉ ከሌላ አገር መምጣቱ የሚያስታውቅ እንግዳ ተከትሏቸው ገባ። እሱም ጥጉን ይዞ ተቀመጠ፡ ከተጠቀለለ ጨርቅ ውስጥ ዳቦና ስጋ አውጥቶ መብላት ጀመረ።

"ሰውየው አንድ ጉርሻ ቆርሶ በጎረሰ ቁጥር ሳላስበው አፌን ከእሱ እኩል እያላመጥኩ ምነው እኔም የምበላው ባገኘሁ!" እል ነበር ሲሉ ራሳቸው ያሳለፉትን ሁኔታ ያስታውሳሉ። "ነገሩን ስደጋግመው ነፍሴን መለስ አደረግኩና 'ትእግስት አልባ አትሁኚ ነፍሴ ሆይ፡ አላህ ላይ እምነትና ተስፋ ይኑርሽ' ብዬ ራሴን ተቆጣሁ" ይላሉ።

ትንሽ እንደቆየ ሰውየው መጣና ከሚበላው አካፈላቸው፡ ይቅርብኝ አሉ። አይሆንም አብረን እንብላ ሲላቸው እሺ ብለው ተቀበሉት። እየተመገቡ ሳለ እንግዳው ስለማንነታቸው ጠየቃቸው፡ "ከጂላን እውቀት ፍለጋ የመጣሁ ነኝ..." ብለው ስለራሳቸው ነገሩት። ሰውየው ተገረመ፡ እኔም ከጂላን ነው የመጣሁት አለና አብዱልቃድር የሚባል ሰው ያውቁ እንደሆን ጠየቃቸው። "አብዱልቃድር ጂላን ማለት እኔ ነኝ" አሉት። አይኖቹ በእንባ ተሞሉ፤ እያለቀሰ "እባክህን ይቅርታ አድርግልኝ ያንተን ሐቅ ነው የበላሁት"

ጂላንዩ ሰውየው የሚናገረው አልገባቸውምና ዝም አሉ

Edit with WPS Office

"ከጂላን ስወጣ አንዲት አዛውንት አገኘሁ፡ 'ለልጄ አድርስልኝ በግዳድ ከተማ ይማራል' ብላ ስምንት ዲርሃም ሰጠችኝ። አሁን እየበላሁት የነበረው ምግብ እናትህ ከላከችልህ ስምንት ዲርሃም ቀንሼ ገዝቼበት ነው፡ ረጅም ጊዜ ፈልጌ አጣሁህ፣ በግዳድ የምቆይበት ጊዜ ረዘመብኝ፣ ሁኔታውን ከድርቁ ጋር መቋቋም አቃተኝ፣ ከአደራ ገንዘቡ ወስጄ ምግብ ገዛሁበት። እኔ አይደለሁም የመገብኩህ አንተ ነህ ያበላኸኝ። አደራዬን ስላልጠበቅኩ እባክህ ይቅር በለኝ" አላቸው

ደግነቱንና ታማኝነቱን አድንቀው አመሰገኑት፡ የተቀሩትን ዲርሃሞችና ምግቡንም አስይዘው ሸኙት። ከራሳቸው በላይ ለሰዎች ሲያስቡ፣ ከፍላጎታቸው ይልቅ ለሰዎች ቅድሚያ ሲሰጡ አጀብ! ያሰኛሉ። የራስን ነፍስ ውትወታ አሸንፎ ለሌሎች መኖር ተሰውፍ በዋነኝነት ከሚያስተምራቸው ተርቢያዎች መካከል ነው።

****

ሸኽ አብዱልቃድር በ11ኛው ክ/ዘመን (እ.ኤ.አ) እንደመኖራቸው እንደ ታላቁ ኢማም አልገዛሊ በርካታ ፈተናዎችን ማለፍ ነበረባቸው። እጅግ በርካታ የፍልስፍና፣ የክህደት እንዲሁም የፖለቲካ ቀውሶች ኢስላምን በአራቱም አቅጣጫ እየወጋ ያለበት ዘመን። የዐባሲዮች ስርወ መንግስት ሀይል መፈረካከስ እየታየበት ነው። የዲን

Edit with WPS Office

ትምህርቶች እንደ ቀድሞዎቹ የመዝሃብ አባቶች ፈለግ የጠለቀ ምርምርና ጥናት አይታይባቸውም። ለእያንዳንዱ የሀይማኖት እንቆቅልሽ ወይም ወቅታዊ ችግር ከመቶ ዓመታት በፊት የተሰጡ ፈትዋዎችን በማገላበጥ ላይ የተዋቀረ የኢማሞች ህብረት ነው የሚገኘው። ሱልጧኑል አውሊያእ አብዱልቃድር ጂላን ይህ ስርዓት መታረም እንዳለበት ያምኑ ስለነበር የመፍትሄ ሀሳቦችንና ማስተካከያ መንገዶችን እየጠቆሙ ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገው በአላህ ፍቃድ ማሳካት ችለዋል።

ከሸሪዓ እውቀት በኋላ

መድረሳ ከሚወስዱት የሸሪዓን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ጥልቅ የሆነውን መንፈሳዊ እውቀት መፈለግ ጀመሩ። ይህን መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት ወደ ሸይኽ ሐምማድ ቢን ሙስሊም አል-ደባስ ዘንድ ተመሩ። በግዳድ በሰዎች የተጨናነቀች ከተማ ነበረች። ሸይኽ አብዱልቃድር በኖሩበት ዘመን አንድ ሚሊየን የሚሆን ህዝብ ብዛት ነበራት። ጂላንዩ ከዚህ ግርግር አረፍ ማለት ሲፈልጉ ከተማዋን ለቀው ይወጣሉ። ሰላም ይነሳቸዋል። በራሳቸው አንደበት ሲተረክ

"አንድ ወቅት ላይ በግዳድን ጥዬ ለመውጣት ወሰንኩ፡ ከተማዋን ለቅቄ ልወጣ ስል አንዳች ሀይል ገፍትሮ ወደኋላ ጣለኝ

Edit with WPS Office

"ከዚህ አትሂድ፡ የአላህ ባሮች ካንተ የሚጠቀሙት አልለ" ከማይታይ አካል ድምፅ ሰማሁ

"ሰዎችን ምን አደርጋቸዋለሁ፡ እኔ ኢማኔን ነው መጠበቅ የምፈልገው" አልኩ ስጋቴን አውጥቼ

"በላጩ መቆየትህ ነው፡ ለእምነትህ አትፍራ ዋስትና ተሰጥቶሃል" ተባልኩኝ። በማግስቱ ጎዳናዎች ላይ ስዟዟር አንድ ሰው በሩን ከፈተና "አብዱልቃድር ሆይ፡ ትናንት ከፈጣሪህ ምንድነው የጠየቅከው?" አለኝና በሩን መልሶ ዘጋው። ትንሽ ከተጓዝኩ በኋላ መሳሳቴ ገባኝ፡ 'ይህ ሰው ወልይ ነው ባይሆን ኖሮማ ትናንት እኔ ላይ የተከሰተውን ሊያውቅ አይችልም' ብዬ ተመልሼ በሩን ፍለጋ ብሄድም ላገኘው አልቻልኩም። በየሄድኩበት እሱን ፍለጋ ማሰስ ጀመርኩ፡ ከብዙ ጥረት በኋላ አንድ ቀን በሰዎች ስብስብ መሃል አገኘሁት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሸይኼና መንገድ መሪዬ ሐምማድ ኢብን ሙስሊም አል-ደባስ ሆነ" ይላሉ። ተሰውፍን ከርሳቸው ተማሩ።

አንድ ቀን ሸይኽ አብዱልቃድር ከሙርሺዳቸው ሸይኽ ሐማድ ጋር መንገድ እየተጓዙ ነበር። ቀኑ ጁሙዓ ነው፡ በድንገት ሸይኽ ሐምማድ ጂላንዩን ወደ ወንዙ ገፍትረው ጣሏቸው። ሰዎች ሁላ ደንግጠው ቀሩ። ሸይኽ አብዱልቃድር መላ አካላቸው ውሃ ውስጥ ተዘፍቆ በስብሰዋል፡ ምነው ሲሏቸው

Edit with WPS Office

"ቂኑ ጁሙዓ ሆኖ ሳትታጠብ እንዴት ትወጣለህ?" ሲሉም ወቀሷቸው። ሸይኽ አብዱልቃድር ተቻኩለው የጁሙዓን ሱና ዘንግተው ነበር። ሸሪዓ ላይ ጥንቁቅና ጥብቅ መሆንንም ከሸይኻቸው አል-ደባስ ወስደዋል። ወደ አላህ መድረስ የሚፈልግ በጠቅላላ ሙርሺድ ሸይኽ ያስፈልገዋል። አንድ ቀን ሰዬዱና ዐልይ ነብያችንን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ወደ አላህ በሚደረገው ጉዞ ቀላሉ መንገድ የትኛው ነው? ብለው ጠየቋቸው። "ዐልይ ሆይ፡ አንድ የአላህ ወዳጅ ፈልግና በሱ ጥላ ተጠለል። ጥላው ከሰውየው አይነጠልምና። ያኔ በቀላሉ እና በፍጥነት ወደ ጌታህ መለኮት ትደርሳለህ" አሉት። እርሳቸውም እንዲህ ይላሉ "መንፈሳዊ ደቀ-መዝሙር (ሙሪድ) ስለ ኢማን ብልፅግናው መምህር ያስፈልገዋል፤ በራሱ ለመቆም የሚያበቃ ጠንካራ ኢማን እስኪኖረው ከሸይኹ መለየት የለበትም" ማንም ሸይኽ ያለ ሙርሺድ ሸኽነት ደረጃ አይደርስም። ከእውቀት ምገባ በተጨማሪ ስነ-ምግባርን የሚገራ፣ መንገዱን የሚያመላክት፣ በየእለቱ እንደ ሙሪዱ አቅም ለመንገዱ ብቁ የሚደርጉትን እውቀቶች የሚለግስ ለነብዩ ሙሐመድ ቅርብ የሆነ ሙርሺድ ያስፈልገዋል።

****

የእህል ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት ተማሪዎች አንድ ላይ

Edit with WPS Office

ሰብሰብ ብለው ከበግዳድ አቅራቢያ ካለችው 'ባቁባ' ከተማ ገበሬዎች ዘንድ በመሄድ ካመረቱት ጥራጥሬ ጥቂት እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ። የባቁባ ነዋሪዎች ደረሳዎቹን በፍቅር፣ በደስታና በክብር ተቀብለው ያስተናግዷቸዋል። አንድ ጊዜ ከሸኽ ጂላኒ ጋር አብረው የሚማሩ ተማሪዎች ለቀሪአ ወደ ባቁባ እንውጣ ሲሉ ጠየቋቸው። ጓደኞቻቸውን ላለማስከፋት ሲሉ እሺ ብለው ሄዱ። እዚያ ሲደርሱ ሸሪፍ ባቁቢ የተባሉ ትልቅ የአላህ ወልይ በዛች መንደር እንደሚኖሩ ተነገራቸው። ገውሰል አዕዘም ምርቃታቸውን ለማግኘት ዚያራ ሸኽየው ዘንድ ሄዱ። ሸሪፍ ባቁቢ ሸኽ አብዱልቃድር ጂላንን በተመለከቱበት ቅፅበት የዘመኑ ቁጥብ መሆናቸውን ተረዱና

"ልጄ ሆይ! በአላህ መንገድ ላይ የሚጓዙ ሰዎች እጆቻቸውን ወደ አላህ እንጂ አይዘረጉም። አንተ ከተመረጡት የአላህ ባሮች መካከል ትመስላለህ፤ ስለዚህ ቀሪአ መጠየቅህ ደረጃህን ይፃረራል" አሏቸው። "ከዛን ቀን በኋላ እንደዚህ አይነት ጉዞዎች ላይ ተሳትፌ እና ከሰዎችም ምንም ዓይነት ነገር ጠይቄ አላውቅም" ሲሉ ተናግረዋል።

"ዓለም የተፈጠረችው ለሰው ሲሆን፣ ሰው ደግሞ ለቀጣዩ ዓለም ተፈጥሯል" የሚሉት ሙሕዪዲን አብዱልቃድር ጂላኒ ፍፁም ዛሂድነትን አላስተማሩም፤ ፍፁም የሀብት ክምርም

Edit with WPS Office

አላሳዩም። ሚዛናዊ እይታ ነበራቸው። "በዓለም ላይ ስለሚኖራችሁ የሀብት ድርሻ እንደ ለማኝ ሆናችሁ ለማግኘት አትሞክሩ፤ ይልቁንም ስጦታው ከፊቱ እንደሚቀርቡለት ንጉስ ሆናችሁ ውሰዱ። ይህች ዓለም ከአላህ ፊት ቆመው ለሚጠብቋት አክብራ ትመጣለች፤ ከደጇ ቆመው ለሚማጸኗት ግን አዋራጅ ናት። ስለዚህ በምድር ስለሚኖራችሁ ድርሻ ራሳችሁን አዋርዳችሁ ወይም ክብራችሁን ተነጥቃችሁ ለማግኘት አትሞክሩ። አላህ ከናንተ የሚጠብቀው በክብራችሁ እንድትኖሩ ነው" እያሉ ያስተምራሉ።

ከበጎ ምግባራቸው

ሀድረት አብዱልቃድር ጂላን በባህሪያቸው የተመሰገኑ፣ ያያቸው ሁሉ የሚወዳቸው፣ የታላቁን ነብይ ፈለግ በመከተል ወደር የማይገኝላቸው የድንቅ ስብእና ባለቤት ነበሩ።

አራት ሚስቶች ነበሯቸው፡ ከነሱም አርባ ዘጠኝ ልጆችን ወልደዋል፤ ሀያ ሰባት ወንዶችና ሀያ ሁለት ሴቶች። በአንድ እለት ሚስታቸው መጣቻቸውና ‹‹አንቱ የመልካም ስብእና ባለቤት፡ ትንሹ ልጃችን ሞቶብን ሀዘን ላይ ነው ያለነው። እርስዎ ግን ጠብታ እንባ እንኳን ሲያፈሱ አላየንም። አንዳች የሀዘን ባህሪ ወይም ምልክት አላሳዩም። ለአብራክዎ ክፋይ

Edit with WPS Office

እንዴት አይራሩም?›› ስትል ወቀሳ ቢጤ ንግግር ጣል አደረገች።

‹‹እኛ መከራ ተደራርቦብን ቅስማችን ሰብር ብሏል፡ እርስዎ ግን ምንም እንዳልተፈጠረ ነገር ወደ ተለመደው ተግባርዎ ይሄዳሉ። መምህራችንና መሪያችን ነዎት፡ ነገር ግን ልብዎ እንደዚህ ደንዳና ሆኖ እዝነት ካጣ በፍርዱ ቀን ያድኑናል ብለን ተስፋ የምናደርገው እኛስ እንዴት በእርስዎ ልንተማመን እንችላለን?›› ብላ ብሶቷንና የተሰማትን ቅሬታ አውጥታ ተናገረች።

ሸይኹም ዝም ብለው ሲያደምጧት ቆይተው እንደሚከተለው መለሱ

‹‹ውድ ባልደረቦቼ! ይህ ሰው ልቡ ደንዳና ነው ብላችሁ በፍፁም አታስቡ፤ እኔ እምነት ለሌለው ሰው አማኝ ባለመሆኑ እራራለታለሁ፣ ለሚነክሰኝ ውሻ አዝኜ ዱዓ አደርጋለሁ፣ ሰዎችን መናከስ እንዲያቆም እለምነዋለሁ፣ የኔ መነከስ እያሳስበኝም፤ ሰዎች ውሻው ላይ ድንጋይ መወርወር እንዲያቆሙ ስል ነው። ለዓለማት እዝነት አድርጎ ከላካቸው ነብይ የወረስኩት ድርሻ እዝነት መሆኑን ዘንግታችሁት ነው?›› አሉ ባለቤታቸው ‹‹በእርግጥ እናውቃለን፡ ታድያ ለነከሰዎት ውሻ የሚራራ ልብ ካለዎት፡ እንዴት በሞት ለተነጠቁት የገዛ ልጅዎ የሀዘን ስሜት አይሰማዎትም?››

Edit with WPS Office

‹‹ተወዳጆቼ፡ እናንተ ከምትወዱት ልጅ እንደተነጠላችሁ በማሰብ ታለቅሳላችሁ፤ እኔ ግን ሁሌም ከምወደው ጋር ነኝ። እናንተ በዚህች ዓለም በህልም ታዩት ይሆናል፣ በሌላኛው ህልም ግን ታጡታላችሁ። አላህ ‹‹ይህች ቅርቢቱ ዓለም ህልም እንጂ ሌላ አይደለችም›› ይላል፤ ለተኙ ሰዎች በእርግጥም ህልም ናት። እኔ ንቁ ነኝ፤ የጊዜ ዑደት ውስጥ በነበረ ጊዜ ልጄን እንደናንተው አየው ነበር። አሁን ግን ከዛ የጊዜ ዑደት ወጥቶ ለናንተ ቢሰወርም ለኔ ግን ይታየኛል። አብሮኝ አለ። ከዚህ በፊት እንደሚያደርገው ሁሉ አጠገቤ ሆኖ እየተጫወተ ነው። በልቦና አይን እውነታውን መመልከት ስትችሉ ህያው ሆነም ሟች እውነት መቼም አይሰወርም›› ብለው መለሱላት።

የጥሪ መጀመር

496 ዓ.ሂ የሸሪዓ እና የተሰውፍ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ሸይኽ አብዱልቃድር ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ለሀያ አምስት አመታት 521 ዓ.ሂ ድረስ ነፍሳቸውን ከዱንያ አላቅቀው በተመስጦና በመገለል ቆይተዋል። "ሀያ አምስት አመታት በሙሉ የዒራቅን ጫካዎች መኖሪያዬ አደረግኩ፤ አርባ አመታት የፈጅርን ሰላት በዒሻ ውዱ ሰገድኩ፤ አስራ አምስት አመታት በአንድ እግሬ ቆሜ ቁርአንን አኸተምኩ፤

Edit with WPS Office

ከሶስት እስከ አርባ ቀናት ምንም እህል ሳልቀምስ የምቆይባቸው ጊዜያት በርካታ ነበሩ" ይላሉ ሸይኹ። ቀርክ፣ ሹሽታር፣ ቡርጅ አጀሚ፣ አይዋን ቀስራ፣ አልመዳኢን እና ሌሎችም በነዚህ ጊዜያት ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ካረፉባቸው ከተሞች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

****

በግዳድ አካባቢ በጫካዎች መካከል ለተፈኩር እና መንፈሳዊ ከፍታ ልምምድ በሄዱበት አንድ እለት በጣም ውብ፣ ብሩህ መልክ ያለው የአላህ ወዳጅ አገኙ። አብረውት ለመቀመጥ ይፈልጉ እንደሆን ጠየቃቸው። እሳቸውም አዎንታቸውን ገለጹለት። "ትእዛዜን የምትቀበል ከሆነ እና ንግግሬም ሆነ ተግባሬ ላይ ጥያቄ የማታነሳ ከሆነ ብቻ ነው እኔ አብሬህ ለመቀመጥ ፍቃደኛ የምሆነው" አላቸው። እሺ ብለው ተስማሙ። ወደ አንድ ቦታ እየጠቆመ "እዛች ቦታ ላይ ተቀመጥ" አላቸውና ትቷቸው ሄደ። ሸይኻችን እስኪመለስ ድረስ ተቀምጠው እየጠበቁት ነው። ከአንድ ዓመት በኋላ ተመለሰ፤ ሸኽ አብዱልቃዲር ጂላን ቦታው ላይ ተቀምጠው ነበር። ለጥቂት ጊዜያት አብሯቸው ቆየና "ተመልሼ እመጣለሁ: አሁንም ወደየትም ሳትሄድ እንድትጠብቀኝ" ብሏቸው ሄደ። ሌላ አንድ ዓመት ቆየና ተመልሶ መጣ። ለትንሽ ሰዓት አብሯቸው ተቀመጠ። ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ

Edit with WPS Office

እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ተመሳሳይ ትእዛዝ ሰጥቷቸው ሄደ። አንድ ዓመት ቆይቶም ተመለሰ። በአሁኑ ግን ዳቦና ወተት ይዞላቸው ነው የመጣው።

"**እኔ ኸድር ነኝ!** ይህን ማእድ ካንተ ጋር እንድጋራ ታዝዣለሁ" አላቸው። አብረው ተቀመጡና የተባረከውን ምግብ በጋራ ተመገቡ። ኸድር ዐ.ሰ ጠየቃቸው

"አብዱልቃድር ሆይ፡ እዚህ ቦታ ላይ ሶስት ዓመታትን ስትቀመጥ ምን በላህ?"

"ሰዎች የወረወሩልኝን" አሉት

በመጨረሻም የአላህ ፍቃድ ሆነና ሰአቲቱ ደረሰች

ከሸኽ አልሙኸርረሚ ስር ለዓመታት ሙሪድ ሆነው ሐለቃቸውን ሲታደሙ፣ መንፈሳዊ ትግበራዎችን ሲቀበሉ ኖረዋል። ሸኻቸውም ከጂላን ከተማ ለመጡት ለውድ እና ልዩ ተማሪያቸው የነበራቸው ፍቅር ከፍተኛ ነበር። አንድ ቀን ተማሪዎቻቸውን እያስቀሩ እያለ የሆነ እቃ እንዲያመጡላቸው ሸኽ አብዱልቃድር ጂላንን ይልኳቸዋል። እንደወጡም "አንድ ቀን የዚህ ወጣት እግር ከሁሉም የአላህ ወልዮች ትከሻ በላይ ይሆናል። በ'ርሱ ዘመን የሚኖሩ አውሊያኡላህ በጠቅላላ ከፊቱ ይተናነሳሉ" ብለው ዙርያቸውን ከበው

Edit with WPS Office

ለነበሩት ተማሪዎች አበሰሩ። ሸኽ አቡ ሰዒድ አልሙኽርረሚ የጠሪቃውን መሪነት ከሰጧቸው በኋላ በራሳቸው እጅ ምግብ እያጎረሱ አበሏቸው። ሸኽ አብዱልቃድር ጂላንም ይህን ክስተት ሲያስታውሱ "የጠሪቃ ሸኼ ከአፌ በሚያጎርሱኝ እያንዳንዱ ጉርሻ፣ ልቦናዬ በማዕሪፋ ብርሃን ሲሞላ ይታወቀኛል" ይላሉ። ከዚያ በኋላ ሸኻቸው አቡ ሰዒድ ኺርቃ(ካባ) አለበሷቸው "ይህ ኺርቃ ለዓሊ ሙርተዷ ረ.ዐ ከአላህ መልእክተኛ የተሰጠ ነው። ከዓሊ ከ.ወ ለሐሰነል በስሪ ተላለፈ። ከሐሰነል በስሪ ደግሞ ለዘመናት ሲቀባበል ቆይቶ እኔ ጋር ደርሷል" ብለው ከሸኽ ወደ ሙሪድ የሚዋረሰውን የዓለም ሙስሊሞችን የዒልም መሪነት የሚያሳየውን ካባ አልብሰዋቸዋል። ዓሊሞች የነብያቶች ምትክ ናቸውና

****

ወደ በግዳድ ከመመለሳቸው በፊት አንድ ቀን በከተማዋ ጎዳና ላይ ሲጓዙ አንድ ሸማግሌ ያያሉ፡ ህመም እያሰቃየው ሰውነቱ የመነመነ የእድሜ ባለጸጋ ይመስላል። ከመንገዱ ዳር ተኝቶ ሰላምታ አቀረበላቸው። አፀፋውን መለሱለት። መጥተው ሲቀመጥ እንዲረዱት ጠየቃቸው። ደርሰው ደግፈው ሲያነሱት በሽተኛ የነበረው ሰው ፍፁም ጤናማ ሆኖ ሰውነቱም መግዘፍ ጀመረ። ሱልጣኑል አውሊያእ ሁኔታው

Edit with WPS Office

አስደነገጣቸው "እኔ የአያትህ ሀይማኖት ነኝ፡ ታምሜ ሰቆቃ ውስጥ ገብቼ ነበር፡ አላህ ግን ባንተ እርዳታ ምክንያት ዳግም እንድነሳ አደረገኝ" አላቸው። ይህ ክስተት ለጂላንዩ ብዙ ስራ እንደሚጠብቃቸው የጠቆመ ነበር።

ወደ በግዳድ ሲመለሱ ሀምሳ አመት ሆኗቸዋል፡ ያን ጊዜ ነው ሰዎችን ወደ እምነታቸው ለመመለስ ማስተማር የጀመሩት። ከላይ እንደተጠቀሰው ሌላኛው መምህራቸው ሸይኽ አቡ ሰዒድ አልሙኽርረሚ ምትኬ ይሁን ብለው ባቡል ኢጃዛ መድረሳ ላይ ኸሊፋነቱን ሰጧቸው። እዛው መድረሳ ማስተማር ጀመሩ። በርግጥ ማስተማር የጀመሩት በትንሽ ሰዎች ነበር፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ ሰዎች በንግግራቸው እና በባህሪያቶቻቸው እየተማረኩ መድረሳቸውን መቀላቀል ጀመሩ። የበግዳድ ከተማ አብዛኛው ነዋሪ መሻኢኾቻቸውን ጨምሮ የርሳቸው ተከታይ ሆኑ። ሸዋል 521 ዓ.ሂ ላይ ሸይኽ አብዱልቃድር የአላህ መልእክተኛን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በህልማቸው አዩ፡ እውቀታቸውን ለሰዎች ማከፋፈያ ጊዜው እንደደረሰ ተነገራቸው። እርሳቸውም አንደበተ-ርቱእነትን ጠየቁ። ዐጀም/ዐረብ ያልሆኑ ስለነበሩ በዐረብኛ ማስተማር፣ የፈለጉትን መልእክት በትክክል ማድረስ እንዳይቸግራቸው ፈሩ። አያታቸውም "ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ። በዚያችም እርሷ መልካም በኾነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው። ጌታህ እርሱ

Edit with WPS Office

ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው አዋቂ ነው። እርሱም ቅን የሆኑትን ሰዎች አዋቂ ነው" የሚለውን የአላህ ቃል ሰባት ጊዜ ደጋግመው ቀርተው በሸይኽ አብዱልቃድር ፊት ላይ ኡፍፍ አሉት።

የዛን ቀን ከዝሁር ሰላት በኋላ ሚንበር ላይ ወጥተው ለነበሩት ሰዎች መልእክት ማስተላለፍ ጀመሩ። ሰዎቹ ተማረኩ፡ ቃላቶቻቸው ተዓምር መፍጠር ጀመሩ። ከ521-561 ድረስ በዚሁ መድረሳ አስተምረዋል። የበግዳድና ከተማ ነዋሪዎች እና አጎራባች መንደር ሰዎች እየመጡ ከእሳቸው መማር ጀመሩ። የነበረው መድረሳ ጠበበ፡ ሰዎች ወደ ጎዳናዎች ይፈሱ ጀመር። ከአመታት በኋላ በአካባቢው የሚገኙ መኖርያ ቤቶች ተገዝተው ለትምህርት ማእከሉ ማስፋፊያ ተደረጉ። የአገሩ ነዋሪ ያለውን አቅም አንዳች ሳይሰስት ድሃውም ሀብታሙም፣ ሴቱም ወንዱም ተረባርቦ ተገነባ። ይህ አጋጣሚ ሲታወስ ሁሌም አብሮ የሚዘከር ታሪክ አለ። የበግዳድ/ዒራቅ ነዋሪ፣ ባለሀብት በገንዘቡ ድሃው በጉልበቱ እያገዘ ነበር። ያለምንም ክፍያ ከሚያገለግሉ ሰዎች መሃከል አንዲት ወጣት እንስት ነበረች፤ ባለቤቷን ወደ ስፍራው ይዛ መጥታ ሸይኹ ጋር አቀረበችና "ባለቤቴ ነው፣ ሀያ ዲናር/የወርቅ ሳንቲሞች ለመህር ሰጥቶኛል። ግማሹን እንዲሁ በነፃ እመልስለታለው፤ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ እዚህ እያገለገለ ለሰራበት እንዲከፈለው ላደርግ ነው ይዤው

Edit with WPS Office

የመጣሁት" አለቻቸው። ሁሉም በዚህ መልካም ንግድ ተስማሙ። ሚስትየው ወርቆቹን ለሸይኽ ዐብዱልቃድር ጂላን አስረከበች፤ ባልየውም በመድረሳው ግንባታ ላይ አሻራውን ማኖር ጀመረ። ገንዘቡ ተከፍሎ ሲያልቅ ግን እሱም ስራውን አልተወም፤ ሸይኹም ክፍያቸውን አላቋረጡም። ምክንያቱም ከጅምሩ እንዳይሰራ ያገደው ድህነት እንጂ ተግባሩን ቸል ብሎ አለመሆኑን ያውቁ ነበርና ነው።

ተከታዮቻቸው

በዚህ መልኩ ሸይኽ አብዱልቃድር ሰዎች ዘንድ በፍቅር በር መግባት ቻሉ። ስነ-ምግባራቸውና ትምህርታቸው በአብዛኞቹ ነዋሪዎች ተወዳጅ ሆኖ ቀጠለ። ተማሪና ተከታዮቻቸው እጅግ ተበራከቱ። ሁሉንም እንደፍላጎቱና እንደአቅሙ የማሳመን ችሎታ አላህ ሰጥቷቸዋል። የሰው ልጅ ያለውን መንፈሳዊ ተፈጥሮ በመጠቆም በቁሳዊ ዓለም ውስጥ እንዳይዘፈቅ መክረዋል። ከፊታቸው ቀርቦ ስብከታቸውን የሰማ ማንኛውም ሰው ልቡ እንደሚከፈት ታሪካቸውን በቅርበት ያጠኑ ሁሉ በአንድ ድምፅ ይመሰክራሉ። ከተሰጧቸው ተዓምራት መካከል ትልቁን ስፍራ የሚይዘው ይኸው በሰዎች ልብ ውስጥ የጠፋን የኢማን ብርሃን ማቀጣጠል መቻላቸው ነው።

አብዱሰመድ ኢብኑ ሁማም በጊዜው በግዳድ ውስጥ ከነበሩ

Edit with WPS Office

ባለባቶች መካከል ቅድሚያ ተጠሪ ባለሀብት ነበር። የቅርቢቱ ዓለም ሰው፤ ኩራተኛ ነበር። የያዛቸው ሀብቶችና በስሩ ያሉ ሰራተኞች ሁሉ እንደ የግል ንብረቱ አድርጎ የሚያስብ እብሪተኛ ሰው። ኢብኑ ሁማም ሁሉ ነገራቸውን መቆጣጠር እንደሚችልና ያሻውን ሊሰራባቸው እንደማይሳነው ያምን ስለነበር ሰዎች ብዙ አይወዱትም።

በሸኽ አብዱልቃድር ጂላኒ ዘመን ነበር የሚኖረው፤ ነገር ግን ታላቁን ሸይኽ ይጠላቸው፣ አላህ የሰጣቸውን ተዓምራትም ያስተባብል ነበር። ታሪኩ በራሱ እንደሚከተለው ተተርኳል

‹‹እንደምታውቁት እኚህን ሸኽ እንድም ቀን ወድጃቸው አላውቅም። የብዙ ንብረት ባለቤት ብሆንም፣ የተመኘሁትን ሁሉ ባደርግም ረክቼ፣ ተደስቼና ሰላም ሁኜ አላውቅም ነበር። አንድ ቀን ጁሙዓ በሳቸው መድረሳ በኩል እያለፍኩ ሳለሁ የአዛን ጥሪ ተሰማ፤ ለራሴ እንዲህ አልኩት፡ ‹‹እስቲ ይህን ባለ ተዓምር ሰውዬ እንየው፡ ከርሱ ዘንድ ገብቼ ልስገድ፤ በዛውም በንግግሩ ወይ በተዓምሩ ሰዎችን እንዴት እንደሚማርክ አያለው›› ብዬ ወደ ውስጥ ዘለቅኩኝ።

መስጂዱ በሰዎች ታጭቋል፤ እንደምንም ተጋፍቼ ከፊትለፊት ደረስኩና ከሚንበሩ እግር ስር ቦታ አግኝቼ ተቀመጥኩ። ሸይኹ ኹጥባቸውን መስበክ ጀምረዋል። የሚናገሯቸው ንግግሮች ሌሎችን እያስደሰቱ እኔን ደግሞ እያበሳጩኝ፣

Edit with WPS Office

እየተናደድኩ ነበር። ከፍተኛ ድካም ተሰማኝና ራሴን ማሳረፍ ፈለግኩ፤ ነገር ግን ከመስጂዱ መውጣት የማይታሰብ ሆነ። ማምለጫ መንገድ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ስማትር ጠጠር መጣያ ቦታ እንኳን ሳይተርፍ ቦታው በሰዎች ተጨናንቆ አየሁ። አሁን ለሸኽየው የነበረኝ ጥላቻ ይብስ ጨመረ።

በዚያው ቅፅበት ሸኽ አብዱላቃድር በእርጋታ ከሚንበሩ ደረጃዎች ወርደው ከፊቴ ቆሙ፤ ኹጥባ ማድረጋቸውን አላቆሙም። እኔን ግን በረጅሙ ካባቸው ሸፈኑኝ። ወዲያውኑ ራሴን እጅግ ውብ በሆነ አረንጓዴ ሸለቋማ ስፍራ ውስጥ አገኘሁት። ንፁህ ጅረት ይፈሳል፣ ነፋሻ አየር ይነፍሳል፤ ከኔ ውጪ ማንም አልነበረም። አሁን ውስጤ ተረጋጋ፡ በቂ እረፍት አድርጌ፣ ታድሼና ከውሃው ዉዱ አድርጌ ሰላት ልቆም ስል፡ ሸይኹ ካባቸውን ከላዬ ላይ አነሱ። አሁን ደግሞ ራሴን ከሳቸው መስጂድ ውስጥ አገኘሁት፤ ቀስ እያሉ ከወረዱበት ሚንበር ወጥተው የጁሙዓ መልእክታቸውን ማስተላለፍ ቀጠሉ።

በተከሰተው ነገር ተገርሜያለሁ፤ ወገቤ ብቻ ሳይሆን ልቤም ጭምር እርፍ ብሏል። ቅድም የነበሩብኝ ቅሬታዎች፣ ቁጣዎችና መጥፎ ስሜቶች ሁሉ ብን በለው ጠፍተዋል።

ሰላት ከተሰገደ በኋላ ከመስጂዱ ወጥቼ ወደ ቤት አመራሁ፡ መንገድ ላይ ግን የካዝናዎቼን ቁልፍ እንደረሳሁ ታወሰኝ። ወደ

Edit with WPS Office

መስጂዱ ተመልሼ ፈለግኩት፡ ግቢውን በሙሉ አካልዬ ብፈልገውም ላገኘው አልቻልኩም። በዚህ ምክንያት ካዝናዬን ለማስከፈት ከቁልፍ ሰራተኛው ጋር ከባድ ጊዜ ለማሳለፍ ተገደድኩ።

በማግስቱ ለንግድ ጉዞ መውጣት ነበረብኝና ከቅፍለቱ ጋር መጓዝ ጀመርኩ። በግዳድን ለቀን ሶስት ቀናት ተጓዝን። አንድ ቦታ እረፍት ለማድረግ ስንወስን እጅግ ውብ የሆነ ሸለቋማ ስፍራ አገኘን። ቀልብ ወደሚስበው ጅረት አንዳች ኃይል ያስገደደን ይመስል ሁላችንም ተማርከን ወደ ውስጥ ዘልቀን ገባን። እዚህ ቦታ ላይ ካሁን በፊት መጥቼ፣ ከውሃው ታጥቤና መንፈሴን አድሼ መውጣቴን ለማስታወስ በዙ ጊዜ አልፈጀብኝም። ዛሬም እንደበቀደሙ ኩልል ካለው ውሃ ታጠብኩ፤ ወዱእ አድርጌ ዞር ስል የጠፋኝን የካዝና ቁልፍ አየሁት። አዎ ራሱ ነው፡ የካዝናዬን ቁልፍ አገኘሁት። በሆነው ሁሉ ተገርሜ ወደ በግዳድ ስመለስ የታላቁ ሸኽ ጂላን ተከታይ ለመሆን በቃሁ››

ያመጡት ለውጥ

በአንድ ቀን ብቻ 70,000 የሚሆኑ ሰዎች ንግግራቸውን ለማድመጥና መንፈሳቸውን ለማምጠቅ የሚገኙባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ነበሩ። በእውቀትና በጥበብ አዋዝተው

Edit with WPS Office

ሲያስተምሩ ከፊታቸው የተሰበሰቡ ሰዎች ከፊሎቹ እንባ ልብሳቸውን ያበሰብሰዋል፣ ከፊሎቹ ራሳቸውን እየሳቱ ይወድቃሉ፣ በአላህና በመልእክተኛው ፍቅር ቅልጥ ብለው የሚሞቱም በርካታ ነበሩ። የበግዳድ ነዋሪዎች ከሳቸው ስነ-ምግባርና መልካም ስብእና መንፈሳቸውን አምጥቀዋል፤ አብላጫው የከተማዋ ነዋሪ በሳቸው ሰበብ ተውበት አድርጓል። የእስልምናን ህይወት ኑረው ከጣፋጩ ፍሬ አጣጥመዋል። በሁሉም ዘንድ ውድ እና ክቡር፡ እያንዳንዱ ሰው ላይ ተፅእኗቸውን ማሳረፍ የቻሉት እኚህ ታላቅ ሸይኽ ደጋጎቹ ሲወዷቸው አምባገነኖችና መጥፎዎች ደግሞ ይፈሯቸው ነበር። ንጉሳን፣ አማካሪያን፣ ጥበባውያን እሳቸው ዘንድ እየመጡ ግር ያላቸውን ጠይቀው መፍትሄ ያፋልጋሉ።

ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ከብዙ አካባቢዎች ማራኪ ንግግራቸውን ለማድመጥ ይመጡና እስልምና ውስጥ ገብተው ከመመለስ ውጭ አማራጭ ያጣሉ። በርካታ አይሁዳውያን እና ክርስትያኖች በሳቸው ሰበብ የቅናቻውን መንገድ ይዘዋል። ለቁጥር ያዳገቱ ክርስትያንና የሁዳን በሳቸው እጅ ወደ እስልምና ተመልሰዋል። ሰዱዱል አውሊያእ፡ ሸይኽ አብዱልቃድር ጂላን ከእንድ ቄስ ጋር ያደረጉትን ናሙና እንይ፡-

በግዳድ ውስጥ የሚኖር እጅግ ጥበበኛና ታዋቂ ቄስ ነበር።

Edit with WPS Office

በርካታ ተከታዮች ነበሩት፤ ሰማያዊ እምነቶችን ያውቃል፡ ስለ ክርስትና እና አይሁዳ ብቻ ሳይሆን ስለ እስልምናም ጥልቅ እውቀት ነበረው። እስልምናን ተረድቷል፣ ቁርአንን አንብቧል፣ ለአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ክብርና ፍቅርም ታድሏል፡ የመጨረሻውን ነብይ እጅግ አድርጎ ይወዳቸው ነበር።

የበግዳዱ ንጉስ ይህን ቄስ ያከብረው ስለነበር አንድ ቀን እሱና ተከታዮቹ ወደ እስልምና ቢመለሱ የሚለው ምኞቱ እውን እንዲሆን ጥሯል። በእርግጥ ቄሱም እስልምናን መቀበል ይፈልግ ነበር፤ ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ ጥርጣሬ ፈጥሮበታል። ሙሉ በሙሉ አምኖበት እንዳይሰልም ያደረገው፡ ሊቀበለው ወይም ሊርረዳው ያልቻለው አንድ እውነት፡ የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወኣሊሂ ወሰለም በአካል ከሰማየ ሰማያት አልፈው ሚዕራጅ ያደረጉትን ጉዞ ነበር።

የሚዕራጅ ጉዞ በአንድ ለሊት ነበር ተጀምሮ የተፈፀመው፤ የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም በአካልና በመንፈስ ከመዲና ተነስተው እየሩሳሌም፡ ከዚያ ደግሞ ወደ ሰባቱ ሰማያት ያዩትን ሁላ ወዳዩበት ቦታ ተጉዘዋል። ጀነትና ጀሀነምን ተመልክተዋል፤ ከዚም አልፈው ጌታቸውን ተገናኝተው 90000 ቃላቶችን አውርቷቸዋል። ያዩትን ሁላ

Edit with WPS Office

አይተው፡ የሆነው ሁሉ ነገር ሆኖ ሲመለሱ ግን የመኝታ ፍራሻቸው ሙቀት ገና አልበረደም ነበር፡ ሁሉም የሆነው በቅፅበታዊ ጊዜ ነው።

ይህን ሁነት የቄሱ አዕምሮ ሊቀበለው አልቻለም፡ ረሱሉላህ ሰለላሁ ዐለይሂ ወኣሊሂ ወሰለም የሆነውንና ያዩትን መተረካቸውም አላሳመነውም። ንጋት ላይ ለሰዎች ስለ ሚዕራጅ ሲናገሩ በርካታ ሙስሊሞች አላመኗቸውም ነበር። እስልምናን ለቀው የወጡ ሰዎችም ነበሩ። በርግጥ ይህ የትክክለኛ እምነት መፈተኛ፡ እውነተኛ አማኞችን ማበጠርያ ክስተት ነበር፡ አሁንም ነው። አዕምሮ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለመቀበል ይቸገራል።

የበግዳዱ ንጉስ ዓሊሞችና ጥበበኞችን ከዚህ ቄስ ጋር እያገናኘ እንዲያሳምኑት ጥረት ማድረጉን ቀጥሏል፡ ነገር ግን ማናቸውም ጥርጣሬውን አስወግደው በሰውየው ልብ እምነት ማስረፅ አልቻሉም። አንድ ምሽት ይኸው ንጉስ ለሐድረት አብዱልቃድር ጂላኒ መልእክት ሰደደ፡ ይህን ቄስ የሚዕራጁን ጉዞ እንዲያምን ያደርጉ እንደሁ ብሎ። ሰዪድ አብዱልቃድር መጥተው ወደተጠሩበት ሲገቡ ንጉሱና ቄሱ ቼዝ እየተጫወቱ ደረሱ። ቄሱ አንድ የቼዝ ጠጠር አንስቶ ሊያስቀምጥ እንደያዘ፡ እርሳቸው በር ላይ ደርሰው ሲገቡ አይን ለአይን ተጋጩ። ቄሱ አንድ ጊዜ አይኑን አርገበገበ፤ ልክ

Edit with WPS Office

ጭፍን አድርጎ ሲገልጠው ጥልቅ ወንዝ ውስጥ ደራሽ ውሃ እያሰመጠው ነው። እርዱኝ እርዱኝ እያለ ይጮሃል፡ አንድ ወጣት እረኛ ሊያድነው መጣና ውሃው ውስጥ ተወርውሮ ገብቶ ህይወቱን አዳነለት። አስደንጋጩ ክስተት ደግሞ ቀጥሎ የሆነው ነበር። እረኛው ተሸክሞ ሲያወጣው፡ ቄሱ ራሱን ዝቅ ብሎ ሲመለከት እርቃኑን ነበር፤ ያስደነገጠው ግን መራቆቱ ሳይሆን ወደ ወጣት ኮረዳ መቀየሩ ነው።

እረኛው ይችን እንስት ካዳናትና ካረጋጋት በኋላ የማን ልጅ እንደሆነች፡ ከየት እንደመጣች ጠየቃት፡ ከበግዳድ ነው የመጣሁት አለች። በግዳድ ከዚህ ከተማ ርቀቱ የወራት ጉዞ እንደሚፈጅ ነገራት፡ ወደ ቤቱ ወስዶ አንከባክቦ ያኖራትም ጀመር። የምትሄድበትና የምታውቀው ማንም ሰው ስላልነበራት ከእረኛው ጋር ተጋብተው መኖር ጀመሩ። ሶስት ልጆችንም አፍርተው ለማእረግ በቁ።

ከብዙ ጊዜያት በኋላ ይች ሴት ከዛው ወንዝ ዳርቻ ልብስ እያጠበች ሳለች ጭቃ አዳልጧት ወደቀች፡ ደራሹ ውሃ ይዟት ሄደ፡ አንድ ቦታ ላይ አሳረፋት፡ አይኗን ገለጠች... ቄሱ ከንጉሱ ጋር ቼዝ የሚጫወትበት ክፍል ተቀምጧል። አንድ ፍሬ የቼዝ ጠጠር ይዞ ሸይኽ አብዱልቃድር ጋር እየተያዩ ነው። ‹‹የተከበርከው ቄስ ሆይ፡ አሁንም አታምንም?›› አሉት። ቄሱ በተፈጠረው ነገር ግራ ተጋብቶ ህልም ነው ምንድን ነው?

Edit with WPS Office

እያለ ያስባል፡ ዝም ብሎ በውስጡ ሲያሰላስል ሸይኽ ጂላኒ መለሱለት፡ ‹‹ምን ማለትህ ነው! ምናልባት ቤተሰቦችህን ማየት ትፈልግ ይሆናል›› አሉና ወደ በሩ ጠቆሙት። በሩ ተከፈተ፡ አንድ እረኛና ሶስት ልጆች ቆመው ተመለከተ። ቄሱ በዚህ ድንቅ ክስተት ስለ ‹ጊዜ› የነበረው ሀሳብ ተቀየረ። ለአላህ የማይቻል ምንም ነገር እንደሌለ ተቀበለ፡ በሚዕራጅ ጉዞም አመነ። እሱና ወደ 5000 የሚጠጉ ተከታዮቹ በሰዬድ አብዱልቃድር ጂላን እጅ ወደ እስልምና ተመለሱ።

እረፍት የለሽ ትግል

ሐያታቸው በከራማ ብቻ የተሞላ አልነበረም፡ በዳዕዋ እንቅስቃሴያቸው ሰዎችን ወደ መንፈሳዊ ትጋት ሲጠሩ እንዲሁ አይደለም፡ ቀላል መንገዶችንና ስልቶችን እያሳዩ ነው። ብዙ ታግለዋል፡ እጅግ ደክመዋል። ጠንካራ ኢማን ያላቸው ትውልዶች እንዲፈጠሩ የተቅዋ ጠላቶችን ፈትሸዋል። በዲስኩሮቻቸውና በመፅሀፎቻቸው አብራርተውም ለቀጣይ ትውልድ አሻግረዋል።

በጊዜው ለነበረው መሰናክል መፍትሄ ለማበጀት ቅድሚያ ችግሩን ከመሰረቱ አጠኑ። የበግዳድ ነዋሪዎች ልቦና በፍርሃት ተሸብቦ አገኙት። ሁኔታው ስላላማራቸው ጠጋ ብለው ይበልጥ ለመረዳት ሞከሩ፡ ብዙዎቹ በነበረው

Edit with WPS Office

ፖለቲካዊ ቀውስ የተረበሹ ናቸው። ከአላህ ይልቅ ገዢዎቻቸውን አብዝተው የሚፈሩ፣ በተልፈሰፈሰ ልቦና የተሞሉ ዜጎች በስፋት ይታያሉ። የዚህን ጋሬጣ ስረ-መሰረት በማስረዳት ተጠመዱ። ህዝቡ በሐዲስ፣ በተፍሲርና ሲባዳዊ እንቅስቃሴው የነበረው ጠንካራ መንፈስ ተዳክሟል። ስለሚያጋጥመው ችግር በአምላኩ ላይ የነበረው ፅኑ እምነት ጠውልጓል።

ህዝብ በስልጣን ጥመኞች ሸኩቻ የደረሰበት በደል ኢማኑን ጭምር እየፈተነው መሆኑን ጂላንዩ ተረድተዋል። ይህን የማህበረሰብ ችግር ለመፍታት የሚችሉትን ሁሉ የዳዕዋ ተጋድሎ አደረጉ፡ ስለ ተቅዋ ሰበኩ፡ ሰዎች ወደ አላህና መልእክተኛው ቢመለሱ መንገዱ ቀላል እንደሚሆን አሳዩ። በህይወታቸው አንድም ቀን ንጉስ ወይም ባለ ማ'ረግ መጣ ብለው ከመቀመጫቸው ተነስተው የተለየ ክብር አሳይተው አያውቁም። በየዳዕዋ መድረኮቻቸው የሚታደመውን ሰው መንፈስ በዚህ መልኩ መመገብ ተያያዙት።

"በልብ ውስጥ ያለ የኢማን ከፍታ በወረደ ጊዜ የድል አድራጊነትና ጀግንነት መንፈሶች ይሰለባሉ" እያሉ አማኞችን መከሩ። በስነ-ልቦና አሰልጥነው አጀገኑ። ወደ ኢማን ብርሃን መሩ። በዚህ መንገድ ለወቅታዊ ችግሮች ወቅቱን ያማከለ መፍትሄ አበጅተው ሰዎች አላህን እንዲይዙ አደረጉ።

Edit with WPS Office

ሲልሲላ

ሸይኽ አብዱልቃድር ጂላን እስከ ነብያችን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ድረስ የሚደርሰው ሲልሲላቸው እንደሚከተለው ነው

ሸይኽ አብዱልቃድር ኢብን ሙሳ

የሸይኽ አቡ ሰዒድ አልሙኽረሚ ተማሪ

የሸይኽ አቡልሐሰን አሊ ኢብን ሙሐመድ አልቁረይሺ ተማሪ

የሸይኽ አቡል ፈረሕ ጡርጡሲ ተማሪ

የሸይኽ አብዱልዋሂድ አልተሚሚ ተማሪ

የሸይኽ አቡበክር አብደላህ ሺብሊ ተማሪ

የሸይኽ ጁነይድ አልበግዳዲ ተማሪ

የሸይኽ አቡልሐሰን ሳሪ አልሰቀጢ ተማሪ

የሸይኽ ማዕሩፍ አልቀርሂ ተማሪ

የሸይኽ ዳውድ ጣዒ ተማሪ

የሸይኽ ሐቢብ አልአጀሚ ተማሪ

Edit with WPS Office

የሸይኽ ሐሰነል በስሪ ተማሪ

የሰይዱና ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ ተማሪ

የአሸረፈል ኸልቅ ሙሐመድ ኢብን አብደላህ የመጨረሻው ነብይ ሶሃባና ኸሊፋ

ስንብት

91 አመታትን ዱንያ ላይ ቆይተው አላህ ሩሃቸውን ሊወስድ ሲፈልግ ህመም አመጣባቸው። ልጃቸው ሸይኽ አብዱልዐዚዝ ምን እንዳመማቸው ጠየቃቸው

"ማንም አያውቅም" አሉት

"ሰውም፣ ጂንም ሆነ መላኢካ በሽታዬን አውቆ የሚርረዳ የለም፡ የአላህ እውቀት በአላህ ትእዛዝ አይቀንስም። ትእዛዙ ይቀየራል እንጂ እውቀቱ አይቀየርም። ትእዛዙን ይሽር ይሆናል፡ እውቀቱ ግን በፍፁም! ለሞት ሰበብ ይልክና የፈለገውን ይሰራል፡ የመፅሀፉ መሰረት እርሱ ጋር ነው" አሉ። ቀጥለውም "ከሚሰራው ሁሉ አይጠየቅም። እነርሱ (ፍጥረቶቹ) ግን ይጠየቃሉ" የሚለውን የአላህ ቃል አነበቡ። ሌላኛው ልጃቸው ሸይኽ አብዱልጀባር "ከሰውነትዎ የት ቦታ ህመም ይሰሞዎታል?" ሲል ጠየቃቸው፡ "ከልቤ በስተቀር መላ ሰውነቴ ታሟል፤ እሱ (ልቤ) ከአላህ ጋር ሆኖ ህመም

Edit with WPS Office

አያገኘውም" አሉ። 561 ዓ.ሂ በ91 አመታቸው ረቡዑል ሳኒ 11 ወደ ኣኺራ ተሻገሩ።

ፉቱሕ አልገይብ፣ አልፈትሑል ረባኒ፣ ሲረል አስራር፣ አልጉንያ፣ ኸምሰተ ዓሸረ መክቱበን፣ አልፉዩዷት አልረባኒያ እና በሻኢረል ኸይራት ከፅሁፍ ስራዎቻቸው መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የሚጎበኙት መቃብር ከመድረሳቸው ክፍሎች ውስጥ ይገኝ ነበር። ዶሪሃቸው በ941 ዓ.ሂ ዒራቅ ውስጥ ከሚገኙ ጉልላቶች መካከል ትልቅ፣ ነጭና ማራኪ ተደርጎ ተገነባ። ከተማዋ ውስጥ ከሩቅ ይጣራል፤ ከአጠገቡ ሌሎች ጉልላቶች እየተጨመሩና እየታደሱ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ ዘልቀዋል። ይህ ሙዚየም ዒራቅ ውስጥ ከሚገኙ ቅዱስ ስፍራዎች በዋነኝነት ይጠቀሳል፡ 1100 ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል መስገጃ ስፍራ አለው። ሁለት ትይዩ ህንፃዎች፣ 66 ዘመናዊና ሙሉ እቃ የተሟላላቸው ክፍሎች ሸይኹን ለመዘየር የሚመጡ ሰዎችን ያስተናግዳሉ። በየጁሙዓ ለሊት ዚክር የሚደረግባቸው ክፍሎች አላህን በማውሳትና በማመስገን ይደምቃሉ። በየአመቱ ደግሞ የመውሊድ (ለነብዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ልደት) ቀን በሰዎች ተሞልተው መልእክተኛውን እያወሱ፣ ሰለዋት እያወረዱ ያድራሉ።

Edit with WPS Office

ገውስ አብዱልቃድር የተቸገሩትን ምግብ በማብላትም ዝናቸው ናኝቷል፡ ከሐሪማቸው እየተዘጋጀ የሚቀርብ ማእድ ከሳቸው ጊዜ ጀምሮ ለ900 አመታት አልተቋረጠም። በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ከብቶች ለእርድ ይቀርባሉ፡ ምግብ የቸገራቸው መጥተው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው መቆያ የሚያገኙበት ጥንታዊ ኩሽና - መመገብያ "የሸይኽ አብዱልቃድር ኩሽና" በመባል ይታወቃል።

ሰዎች እንደየአቅማቸው ወቅፍ(ስጦታ) ያበረክታሉ። ለሩዝ፣ ለዶሮ እና ለተለያዩ እቃዎች ክምችት ክፍል ተለይቶ ተዘጋጅቷል። ወቅፎች በልዩ መፃፍያ ይመዘገባሉ። በርካታ ሰራተኞች በየቀኑ በአማካኝ 1000 ሰዎችን ይመግባሉ። ከመብልና መጠጥ መስተንግዶ በኋላ ለሸይኽ አብዱልቃድር ሩሕ ፋቲሓ ቀርተው፣ በፍጥረታት አለቃ ላይ ሰለዋት አውርደው ይለያያሉ። የሸይኽ አብዱልቃድር ጂላን ኩሽና በዚህ መልኩ ተደራጅቶ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ደግሞ ከ550 አመታት በላይ አስቆጥሯል።

የቃዲሪያ ጠሪቃ

በህይወት ሳሉ የነበሯቸው ተማሪዎች የዳዕዋ ጥበባቸውን አብዝተው ያደንቁ ስለነበር ኋላ ላይ ለማስተማር ዘዴያቸው ተጠቅመውበታል። በወቅቱ የነበረው ሙስሊም ማህበረሰብ

Edit with WPS Office

በደረሰበት ፖለቲካዊ ኪሳራ መንፈሳዊ ማንነቱም ከሸሪዓ መርሆች እየራቀ ነበር። ይህን ያስተዋሉት ሱልጧኑል አውሊያእ ጂላኒ በፈጠሯቸው ጥበብ አዘል የዳዕዋ ስልቶች በርካቶችን መልሰዋል። ይኸው መርህ በደቀመዛሙርቶቻቸው ተወዳጅ ሆኖ በመቀጠሉ ቀስ በቀስ ፈለጋቸው እንደ አንድ መንፈሳዊ አስተምህሮት መንገድ ሆነ። የቃዲሪያ እንቅስቃሴ ወይም የማስተማር ስልትም ተብሎ ታወቀ።

ሰዩዱል አውሊያእ ካለፉ በኋላ ተማሪዎቻቸው አስተምህሮታቸውን ዒራቅ ውስጥ እና በመላው ዓለመ-ኢስላም አሰራጭተዋል። በ15ኛው ክፍለዘመን መጨረሻ (እ.ኤ.አ) የትምህርት ማእከሎቻቸውን እስከ ሞሮኮ፣ ስፔን፣ ቱርክ፣ ህንድ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ እና ማሊ ማድረስ ችለዋል። የዑስማንያ ስርወ-መንግስት ንጉስ ሱለይማን በግዳድን ከተቆጣጠረ በኋላ (1534) ከፍተኛ ትኩረት ከመንግስት ተችሮት ከመቃብር ስፍራቸው ላይ ትልቅ ጉልላት ተሰርቷል። ትምህርታቸውም በስፋት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተድርጓል።

ኸውጃ አብደላህ የተባሉ አህለል በይት ከሸኽ አብዱልቃድር ተማሪዎች መካከል ናቸው፡ በ1674 (እ.ኤ.አ) ቻይና ድረስ ዘልቀው እስከ እለተ ሞታቸው 1689 ድረስ እስልምናን

Edit with WPS Office

ሲያስተምሩ ቆይተዋል። አሁንም ድረስ ቻይና ውስጥ የሚገኙ ሙስሊሞች እኚህ ሸኽ ይዘው በገቡት የቃዲሪያ ጠሪቃ ይጓዛሉ።

- ሱልጣን ባሁ ምእራብ ህንድ
- ሸይኽ ሲዲ አሕመድ (እ.ኤ.አ 1504 የሞቱ) ካኢ-ወለታ-ቱምቡልቱ፣ አጋዴስና አካባቢዎቿ
- ሸይኽ ሲዲ አልሙክታር አልኩንቲ (1728-1811 እ.ኤ.አ) ሞሪታኒያ፣ መካከለኛው ኒጀር፣ ጊኒ እና አይቮሪኮስት
- ሸይኽ ኡስማን ዳን ፎዲዮ (1754-1812 እ.ኤ.አ) ናይጄሪያ
- ሸይኽ ፈቂህ ሀሺም አልሐረሪ ኢትዮጵያ (1688-1754 እ.ኤ.አ) የቃዲሪያን ጠሪቃ በየዓለም አገራት ካስፋፉ ታላላቅ መሻኢኽ መካከል እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው

ምንጮች

ሸይኽ ቶሱን ቤይሬክ፣ ሲረል አስራር እንግሊዝኛ ትርጉም መግቢያ (የተርጓሚው ማስታወሻ)

ሸይኽ ዐብዱልቃድር ጂላኒ፣ ሙሐመድ አሊ ቡርሃን

WWW.sufiwiki.com

Edit with WPS Office